# የብልጽግና ፓርቲ

## የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት እና የምልመላ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር………/2016 ዓ.ም

(ረቂቅ)

ሚያዝያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ይዘት


**መግቢያ** ........ **1**

**ክፍል አንድ** ........ **2**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች** ........ **2**

አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ ........ 2

አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ ........ 2

አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ ........ 3

አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ ........ 4

አንቀጽ አምስት- የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ የሚመራበቸው መርሆዎች ........ 4

አንቀጽ ስድስት- የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ የተፈፃሚነት ወሰን ........ 4

**ክፍል ሁለት** ........ **5**

**የተኪ አመራር ምልመል መስፈርት፣ ሂደት እና ቋት ማደራጀት** ........ **5**

አንቀጽ ሰባት- የተኪ አመራር ቋት ለማደራጀት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ........ 5

አንቀጽ ስምንት- የተኪ አመራር ምልመላ ሂደት ........ 5

አንቀጽ ዘጠኝ- የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ሂደት ........ 7

አንቀጽ አስር- የተኪ አመራር መረጃ ቋት ስለመከለስ ........ 8

**ክፍል ሶስት** ........ **8**

**በተኪ የአመራር ቋት ማደራጀት ስራ ላይ የሚሳተፉ አካለት ያላቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት** ........ **8**

አንቀጽ አስራ አንድ- ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት ........ 8

አንቀጽ አስራ ሁለት- በየደረጃዉ የሚገኙ ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ........ 8

**ክፍል አራት** ........ **10**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** ........ **10**

አንቀጽ አስራ ስድሰት-  የሴቶች እና ወጣት ሊጎች አባለትን ተኪ አመራር ስለማድረግ ........ 10

አንቀጽ አስራ ሰባት-  ከተኪ አመራር ቋት ስለመታገድ ........ 11

አንቀጽ አስራ ስምንት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የሚስተናገድ ሁኔታ ........ 11

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር ........ 11

አንቀጽ ሃያ- መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ ........ 12

**መግቢያ**

በአገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግናን የማረጋገጥ ራዕይን እውን ለማድረግ በአስተሳሰባቸው፣ በስነ ምግባራቸው፣ በእውቀታቸው፣ በክህሎታቸውና በአፈፃፀም ብቃታቸው የላቁ አመራሮችን በየደረጃው በተኪ አመራር ቋት ለማደራጀት እና ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአመራር ሥርዓት መፍጠር እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ጠንካራ የአመራር ሥርዓት ለመፍጠር መሰረታዊ ከሆኑ ጉዳዮች አንድ በፓርቲው ውስጥ ወደ አመራርነት የሚመጡ አካላት ብቃት ወሳኝ ሲሆን እነዚህን አካላት ለመለየት የሚያስችል አሰራር በፓርቲ ደረጃ ግልፅ በሆነ አግባብ ተቀርፆ ስራ ላይ የሌለ በመሆኑ፣

በፓርቲው ውስጥ ለሚካሄደው የአመራር መተካካት ሂደት ስረዓት ለማበጀት እና በየእርከኑ ተኪ አመራር ሆነው የሚመለመሉ አካለትን በግልፅ፣ ፍትሃዊ፣ አሰታፊና ተጠያቂነት ባለው ሂደት እንዲለዩ በማድረግ ስራውን ተቋማዊና ቀጣይነት ባለው መልኩ በውጤታማነት ማከናወን በማስፈለጉ፣

የተኪ አመራር ምልመለ ሂደት፣ የምልመላ መስፈርት፣ የተኪ አመራር ስምርት እና የባለድርሻ አካላት ሚና በግልጽ በመደንገግ በፓርቲው ውስጥ ከላይ እስከ ታች በቀናጀ መልኩ እንድተገበር ለማድረግ፣ እንዲሁም በሂደቱ ለሚፈጠሩ ክፍተቶች የተጠያቂነት ስርዓትን ማስፍን በማስፈለጉ፣

በፓርቲ ውስጥ የአመራር ቀጣይነትን ለማረጋገጥ እና ወቅቱ ለሚፈልግው የትግል መድረክ ብቁ የሆኑ ተኪ አመራሮችን በመለየት የአመራርነት ብቃታቸውን ሊያሳድጉ የሚያስችሉ አቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 40 መሰረት የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራን ለማካሄድ ያስችል ዘንድ ይህ የተኪ የአመራር ቋት መመሪያ ተዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ አንድ- አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የብልጽግና ፓርቲ የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት እና የምልመላ ማስፈጸሚያ መመሪያ**" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

**አንቀጽ ሁለት- ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "**አባል**" ማለት የብልፅግና ፓርቲን መተዳደሪያ ደንብ እና ፕሮግራምን ተቀብሎ የአባልነት መብትና ግዴታውን የሚወጣ የፓርቲዉ አባል ማለት ነዉ።
2. "**መሰረታዊ ድርጅት**" ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና ከ22 እስከ 210 አባላትን ያቀፈ የሕዋሳት ስብስብ የሆነ አደረጃጀት ማለት ነው፡፡
3. "**ሕዋስ**" ማለት ከ11 እስከ 35 አባላትን ያቀፈ ሆኖ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የአባላት የዕለት ተዕለት አቅም የሚገነባበት አደረጃጀት ነው፡፡
4. "**ግንባር ቀደም አባል**" ማለት ከአባላት መካከል በአመለካከታቸው፣ በስነ-ምግባራቸው፣ በተግባር እንቅስቃሴያቸው እና በአፈጻጸማቸው የተሻሉ ሆነው በአባላት ዘንድ እንዲሁም በአካባቢ ማህበረሰብ በአርአያነት የሚታዩ አባላት ማለት ነው፡፡
5. "**ወረዳ**" ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የወረዳ ደረጃ የተሰጣቸው የአስተዳደር አካላትን ያጠቃልላል::
6. "**ዞን**" ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደሮች፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው::
7. "**ክልል**" ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል::
8. "**አመራር**" ማለት የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆኑ እና በፓርቲዉ አማካኝነት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ በየደረጃው ባለው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች፤ በመሰረታዊ ድርጅት፤ ህዋስ እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በሹመት፣ በምደባ ወይም በምርጫ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የፓርቲዉ አባላት ናቸው።

9. **"የአባል ባህርይ"** ማለት የአንድ አባል አጠቃላይ የአስተሳሰብ፣ የስነ-ምግባር፣ የአመለካከት እና ድርጊት የጋራ ውጤት ነው፡፡
10. **"ተኪ አመራር"** ማለት የፓርቲ አባል ሆነው በግንባር ቀደም አባልነት የተለዩ እና የመሰረታዊ ድርጅትና ህዋስ አመራር ሆነው በቀጣይ በተለያዩ ደረጃዎች ለፓርቲና መንግስት ተልዕኮ ተኪ አመራር ሊሆኑ የሚችሉ አባላትና የፓርቲ አመራሮች ማለት ነው፡፡
11. **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና በፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በተግባር ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው አደረጃጀት ነው።
12. **"የፓርቲ አመራር ኮሚቴ"** ማለት የዋና ጽ/ቤትን ጨምሮ በየደረጃው በብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የፓርቲ ስራዎችን አቀናጅቶ የሚመራ፣ የሚያስፈጽምና የሚፈጽም የአመራር ኮሚቴ ማለት ነው፡፡
13. **"የተኪ አመራር ቋት"** ማለት በየደረጃው ካለው የፓርቲ አደረጃጀት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ከተለዩት አባለት ወይም የመሰረታዊ ድርጅትና ህዋስ አመራር ሆነው በመስራት ካሉ አመራሮች መካከል በአስተሳሰባቸው፣ በስነ-ምግባራቸው እና በአፈጻጸም ብቃታቸው የተሻሉ ሆነው ለተኪ አማራርነት የተለዩት አማራሮች መረጃ ተደራጅቶ የሚቀመጥበት ባንክ ማለት ነው፡፡
14. **"መርህ አልባ ግንኙነት"** ማለት አንድ አመራር የግል ጥቅም ለማግኘት ወይም ሌላውን ለመጥቀም ወይም ሌላ እኩይ ዓላማን ለማሳካት ሲል ከፓርቲ መርሆዎችና እሴቶች ውጭ በሆነና ሕዝብን፣ሀገርንና ፓርቲን በሚጎዳ መንገድ ከሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች የሚያጠቃልል ነው፡፡
15. **"መልካም የፓርቲ ሥነ-ምግባር"** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና አሰራሮችን ማክበርና በጥብቅ መፈፀም እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረ-ገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

**አንቀጽ ሶስት- የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጹት ሃሳቦች በሙሉ የሴት ፆታን የሚያመላክቱ ይሆናል።

## አንቀጽ አራት- የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ ግልፅ፣ አሳታፊና ወጥ የሆነ አሠራር በመዘርጋት የተኪ አመራር ቋትን በማደራጀት የፓርቲን አመራር ለማጠናከር ነዉ።

## አንቀጽ አምስት- የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ የሚመራበቸው መርሆዎች

ተኪ አመራሮችን በቋት የማደራጀት ስራ በሚከተሉት መርሆዎች የሚመራ ይሆናል።

1. የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ እውነተኛ መረጃ እና ማስረጃን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡
2. የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ አሳታፊ፣ አካታች፣ ከወገንተኝነት እና አድሎዓዊነት ነፃ የሆነ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. አንድ አባል ተኪ አመራር ሆኖ ለመመልመል ካሉት የፓርቲ አባላት መካካል በአስተሳሰብ፣ በስነ-ምግባር እና በተሰማራበት የስራ መስክ ውጤታማነቱ ካሉት አባላት ግንባር ቀደም ስለመሆኑ በቅድሚያ መለየትና መረጋገጥ አለበት፡፡
4. የምልመላ ሂደቱ የሴቶች፤ ወጣቶች፣ ምሁራን እና የአካል ጉዳተኞችን ተሳትፎ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል።
5. የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ በየደረጃው ላሉ አደረጃጀቶች ግልፅ እና በግልጸኝነት አሰራርን የተከተለ መሆን ይኖርበታል። አሰራርን ያልተከተለ የተኪ አመራር ቋትን ማደራጀት ስራ ተጠያቂነትን ያስከትላል።
6. የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ እውቀትን፣ክህሎትን እና የተግባር ውጤታማነትን መሰረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።
7. የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ ጥራቱን የጠበቀ፣ መፃኢ የፓርቲያችንን ፍላጎት ታሳቢ ያደረገ እና ለሚፈለገው ዓላማ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል።
8. የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ በአመራር ስርዓታችን፣ በብቃት እና በህብረ-ብሔራዊነት መካከል ሚዛን ለማስጠበቅ የሚያስችል ሊሆን ይገባል።

## አንቀጽ ስድስት- የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት ስራ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በየደረጃው ከፌዴራል እስከ ህዋስ ድረስ ባሉ የፓርቲ አደረጃጀቶች፣ አመራሮች እና አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## የተኪ አመራር ምልመል መስፈርት፣ ሂደት እና ቋት ማደራጀት

### አንቀጽ ሰባት- የተኪ አመራር ቋት ለማደራጀት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

ተቋማዊ መሠረት ያለው፤ ከማንኛውም አድሏዊ አሠራር ነፃ የሆነ፣ ግልፅና ውጤታማ የተኪ አመራር ቋት ማደራጀት በማስፈለጉ የሚከተሉት የምልመላ መስፈርቶች ተዘጋጅቷል፡፡

1. በፓርቲዉ መሰረታዊ እሳቤ ላይ ፅኑ እምነትና አቋም ያለው፤ በህብረ ብሔራዊነት እና በሀገራዊ አንድነት የሚያምን፤ የጠራ አመለካከት ያለው እና ፅንፈኝነትን በፅናት የሚታገል፤
2. ዜጎችንና ህዝቦችን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የህዝብን ጥቅም የሚያስቀድም፣ ከማንኛውም የሙስናና ብልሹ አሠራሮች እንዲሁም መልካም ካልሆነ ስነ-ምግባር ራሱን ያራቀና ሌሎችንም በመገንባት የተመሰከረለት፤ በዚህም በአባላትና በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትን ያተረፈ፤
3. ለአመራርነት የሚበቃው ፍላጎት፣ እውቀት እና ክህሎት ያለው፤
4. የራሱን ሀሳብ ለመግለፅ ሙሉ ነፃነት የሚሰማውና የሌሎችን ሀሳብ ለማስተናገድ የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ ስብዕና ያለው፤
5. በሥራ ሂደት የሚያጋጥሙ አስቸጋሪ ፈተናዎችን የመጋፈጥ ድፍረት ያለውና በአሸናፊነት የመውጣት ብቃት ያለው፤
6. ከሥራው ጋር የተያያዘ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ፤
7. በተሰማራበት የስራ መስክ በተግባር አፈጻጸም ለሌሎች አባላት አርኣያ መሆን የቻለ፡፡
8. በየደረጃው ከሚመለመሉት አመራሮች ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ ቢያንስ ሰላሳ ፐርሰንት (30%) መሆን ይኖርበታል።

### አንቀጽ ስምንት- የተኪ አመራር ምልመላ ሂደት

የተኪ አመራር ምልመላው የብልፅግና ፓርቲ የተኪ አመራር ምልመላ በአንቀጽ 5 ላይ የተዘረዘሩ መርሆዎችን ተከትሎ ከዚህ ቀጥሎ በተቀመጡ ሂደቶች የሚፈፀም ሲሆን፦

1. በቀበሌ ደረጃ

ሀ) በቀበሌ ደረጃ በስራ እና በሚሰጣቸው ተልዕኮ እና ውጤታማ አፈፃፀም ያላቸው፤ የግል ዕቅዳቸውን ወደ ተግባር በመለወጥ ረገድ ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸው፣ ህብረተሰቡን የመምራት እና ማስተባበር አቅም ያላቸው እንዲሁም በፓርቲው ላይ ፅኑ እምነት ያላቸው ከግንባር ቀደም አባላት ለተኪ አመራርነት የሚመለመሉ ይሆናል።

2. በወረዳ ደረጃ

ሀ) በወረዳ /በወረዳ ደረጃ የሚታዩ ከተሞች ለአመራርነት የሚመለመሉ አመራሮች በአመለካከት፤ በሥነ ምግባር፣ በዕውቀት እና በክህሎት የተሻሉ፤ የወረዳውን ነባራዊ ሁኔታ ተገንዝበው ማቀድ አና ማስፈጸም የሚችሉ፤ በሚሰጣቸው ተልዕኮ ውጤታማ የሆኑ እና ፓርቲው ላይ ፅኑ አቋም ያላቸው በወረዳው አስተባባሪ ኮሚቴዎች ይመለመላሉ።

ለ) ለወረዳ ተጠሪ የሆኑ ታዳጊ ከተሞች የሚመለመሉ አመራሮች በወረዳ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመለመሉ ይሆናል።

3. በዞን/በዞን ደረጃ የሚታዩ ከተሞች ደረጃ

ሀ) ዞንና በዞን ደረጃ የሚታዩ ከተሞች የተኪ አመራር የአስተባባሪ ኮሚቴ ምልመላ በክልል/ከተማ አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ የሚመለመል ሲሆን የሌሎች አመራር አባላት ምልመላ ደግሞ በዞኑ/በከተማው አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከናወን ይሆናል።

ለ) የክፍለ ከተማ አስተባባሪ ኮሚቴዎች በከተማው አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከናወን ሲሆን ሌሎች በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚመደቡ አመራሮች ደግሞ በክፍለ ከተማው አስተባባሪ ኮሚቴ አቅራቢነት በከተማ ደረጃ የሚመለመሉ ይሆናል።

4. በክልል ደረጃ

ሀ) በክልሎች፣ አዲስ አበባ ከተማ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚመለመሉ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት በክልሉ/አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ ተመልምለው ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሚቀርብ ይሆናል።

ለ) የክልሎች፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ አባላትና ካቢኔ ያልሆኑ አመራሮችና ምክትል ኃላፊዎች የሚመለመሉት በክልሉ፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ድሬዳዋ አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል።

5. በፌዴራል ደረጃ በምልመላ መስፈርቱ መሰረት የፌደራል ተቋማት አደረጃጀቶች አስተባባሪ ኮሚቴ የተኪ አመራር ምልመላ ስራን በማከናወን ፕሮፋይላቸውን ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

6. መደበኛ የአባላት ግምገማ ስርዓትን ተከትሎ ከአባለት መካከል ግንባር ቀደም አባላት በየግዜው በህዋሳት በጥንቃቄ እንዲለዩ ይደረጋል፡፡

7. አንድ አባል በመስፈርቱ መሰረት ተገምግሞ በግንባር ቀደም ለመሆን በታቀፈበት አደረጃጀት ቢያንስ ለስድስት ወራት በእቅድ ላይ ተመስርቶ በነበረው እንቅስቃሴ መሆን ይኖርበታል፡፡
8. በህዋሳት የተለዩ ግንባር ቀደሞች በመደበኛ የመሰረታዊ ድረጀት ኮንፍረንሶች ላይ ቀርቦ እንዲተችና እንዲጸድቅ ደረጋል፡፡
9. በኮንፍረነሶቹ የጸደቀው የግንባር ቀደሞች ዝርዝር ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በ15ቀናት ውስጥ መስረታዊ ድርጅቱ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት እንዲላክ ይደረጋል፡፡

10. ዝርዝሩ የደረሰው የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የደረሱትን የግንባር ቀደሞች ዝርዝር እና ተኪ አመራር ሊሆኑ የሚችሉ እጩዎች ከአንድ ወር ባልበለጥ ግዜ ውስጥ ሂደቱን በመገምገም ያፀድቃል፡፡

11. የጸደቀው የተኪ አመራሮች ዝርዝር ከተሟላ ግለታሪካቸው ጋር ወደ መረጃ ቋት እንዲገባና መረጃቸው በአግባቡ እንዲደራጅ እንዲሁም ከፍ ላለው ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት የማድረግ ተግባር ይከናወናል፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ- የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ሂደት

1. ካላይ በአንቀጽ ስምንት በተገለጸው መሰረት በየደረጃው የተመለመሉ ተኪ አመራሮች ዝርዝር መረጃ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልል እና በዋና የፓርቲ ጽ/ቤቶች ደረጃ ለአጠቃቀም ምቹ በሆነ ሁኔታ የሚደራጅ ይሆናል፡፡
2. በየደረጃው የተደራጀው የተኪ አመራሮች ዝርዝር የተኪ አመራሮች ባንክ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

3. የተኪ አመራሮችን ቋት የማደራጀት ስራ በየሩብ አመቱ በየደረጃው ባሉ የቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወን ይሆናል፡፡

**አንቀጽ አስር- የተኪ አመራር መረጃ ቋት ስለመከለስ**

በየደረጃው የተደራጀው የተኪ አመራር መረጃ ቋት ተደራሽ፣ ወቅታዊ እና ተአማኒ እንዲሆን በአመት ሁለት ጊዜ መከለስ አለበት።

## ክፍል ሶስት

**በተኪ የአመራር ቋት ማደራጀት ስራ ላይ የሚሳተፉ አካለት ያላቸዉ ተግባር እና ኃላፊነት**

**አንቀጽ አስራ አንድ- ብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

1. በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ፣ ከነባሩ የመረጃ ቋት ጋር የተቀናጀ የተኪ አመራር መረጃ ቋት ማልማት፤
2. ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በተኪ አመራር ቋት ስራ ዓላማ፣ አፈጻጸም ሂደት ላይ ስልጠና መስጠት፤
3. ለክልሎች እና ለከተማ አስተዳዳሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አመራርና ባለሙያዎች የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና መስጠት እና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በቴክኖሎጂ ግብአት ማበልፀግ፤
4. ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ እና ግብረ መልስ መስጠት፤
5. ከክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሚላከዉን መረጃ ማጣራት፤ በአግባቡ ማደራጀት፤ ማስተዳደርና ለታለመለት ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ፤

**አንቀጽ አስራ ሁለት- በየደረጃዉ የሚገኙ ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት**

1. በየደረጃዉ ለሚገኙ ፓርቲ አመራሮች በተኪ አመራር ቋት ስራ ዓላማ፣ አፈጻጸም ሂደት ላይ በየጊዜዉ ግንዛቤ ይፈጥራሉ፤

2. ከታችኛዉ ፓርቲ መዋቅር ተመልምለው የሚለኩ የተኪ አመራር መረጃዎች በመስፈርቱ መሰረት መሆኑን ይከታተላሉ፣ ይደግፋሉ፣ ይገመግማሉ፣ ግብረ-መልስ ይሰጣሉ፣ ትክለኛነቱን ያረጋግጣሉ።
3. የተኪ አመራር ቋት ስራ በተቀመጠዉ የጊዜ ሠሌዳ መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋሉ።
4. የተመለመሉ የተኪ አመራሮችን በአመራር ቋት ውስጥ ያደራጃሉ፤ አንድ ደረጃ ከፍ ላለዉ የፓርቲ መዋቅር በሪፖርት ያሳዉቃሉ፤
5. በክትትል ሂደት ድክመት የታየባቸው ተኪ አመራሮች ሲያጋጥሙ ጉዳዩን በማጣራት ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር በማስደገፍ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ ከተኪ አመራር ቋት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡ከመረጃ ቋት ይሰርዛል

## አንቀጽ አስራ ሶስት- የመሰረታዊ ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት

1. በአባለት ተሳትፎ ከህዋሳት የተመለመሉ ግንባር ቀደም አባለት በምልመላ መስፈርቱ የተለዩ መሆናቸውን ወይም ትክክለኛነቱን በማጣረት ለአባላት ኮንፈረንስ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡
2. የፀደቀውን የተኪ እጩ አመራሮች ሙሉ ፕሮፋል በቅርበት ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በአሰራ አምስት ቀን ወስጥ ሪፖርት ያደርጋል፡፡
3. በየግዜው ከበላይ ተለይተው የሚመጡላትን እጩ ተኪ አመራሮች ዝርዝር በሚቀጥለው ኮንፍረንስ መርምሮ የማጽደው ስራ ይሰራል፡፡
4. የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የጸደቁ የተኪ አመራሮችን እንቅስቃሴ በንቃት ይከታተላል በያ ስድስት ወሩ በተኪ አመራርነት ስለመቀጠላቸው ይሁንታ ይሰጣል፡፡
5. በክትትል ሂደት ድክመት የታየባቸው ተኪ አመራሮች ሲያጋጥሙ ጉዳዩን በማጣራት ከተጨባጭ ማስረጃ ጋር በማስደገፍ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በማቅረብ ከተኪ አመራር ቋት እንዲወጡ ያደርጋል፡፡
6. ከተኪ አመራርነት ጋር የተያያዙ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ አስራ አራት- የህዋሳት ተግባርና ኃላፊነት

1. የመደበኛ የአባላት የግምገማ ወይም የምዘና ስርዓትን ተከትሎ ቢያንስ በስድስት ወር አፈጻጸማቸው ግንባር ቀደም የሆኑ አባላትን እየለየ ለመሰረታዊ ድርጅት ያሰውቃል፡

2. ከህዋሷ አባለት በተኪ አመራርነት ተይዘው ያሉትን አባላት የዘውትር ክትትል በማድረግ ውጤማነታቸውን ያረጋግጣል፤ ችግር ያለባቸው ሲያጥሙ ለመሰረታው ድረጅቱ ያሰውቃል፡፡

**አንቀጽ አስራ አምስት- የተለዩ ተኪ አመራሮች ስለመጠቀም**

1. በሁሉም እርከን ፓርቲ ያለውን የሰው ሃይል አቅምና ተነሳሽነት አውቆ ለተልዕኮ ዝግጁ ለማድረግ ይጠቀምበታል፡፡
2. በግምገማ፣ በተግባር አፈጻጸም፣ በስነ-ምግባር እንዲሁም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ የአመራር ጉድለት ሲያጋጥም በጥንቃቄ አመራር ለመተካት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡
3. ከአሰራር ውጭ በተለምዶ አመራር የመተካት ሂደቶች እንዲቀሩ እና ፓርቲው የጠንካራ አመራር ስብስብ እንዲሆን በማድረግ ውጤታማነቱን ለማሳደግ ያግዛል፡፡
4. አመራር በሚተካበት ጊዜ በተኪ አመራር ልየታ ቅደም ተከተል መሆን አለበት፡፡
5. ተኪ አመራር የመተካት ሂደት በተኪ አመራር ቋት ከተያዙት መካከል በአመራር ምደባ በተቀመጠው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡
6. በተኪ አመራር ፑል ካልተያዘ በስተቀር ወይም በልዩ ሁኔታ ከሙያ ጋር ተያይዞ መተካት ወይም የሚመደብ  አመራር ካልሆነ በስተቀር ከተኪ አመራር ቋት ውጭ በተለምዶ አመራር መመደብ ክልክል ነው፡፡
7. በተለያዩ ምክንያቶች አመራርን በተኪ አመራር መተካት በሚያስፈልግበት ወቅት በተኪ አመራርነት የተመለመሉ ሴት እና ወጣት አመራሮች ቅድሚያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ አስራ ስድሰት-  የሴቶች እና ወጣት ሊጎች አባለትን ተኪ አመራር ስለማድረግ**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የተኪ አመራርነትን ምልመላ ማስፈርት የሚያሞሉ የብልጽግና ሴቶች ሊግ እና እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ የብልጽግና ወጣቶች ሊግ አባላት ተኪ አመራር ሆነው ሊመለመሉ ይችላሉ፡፡

2. በዚህ የተኪ አመራር ምልመላ መመሪያ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሞሉ የብልጽግና ሊግ አባላት በሊጎቹ የአደረጃጀት እርከን ተመርጠው ለሚንቀሳቀሱበት የአካባቢ ቅ/ጽ/ቤት እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡
3. የተኪ አመራር ምልመላው የቀረበለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የቀረበላትን ዝርዝር መስፈርቱን እና ሂደቱን የጠበቀ መሆኑን በመመርመር በየደረጃው ባለው የፓርቲ አመራር ኮሚቴው እንዲጸቅ ያደርጋል፡፡
4. በደረጃው ያለው የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት በአመራር ኮሚቴው የጸደቀው ዝርዝር በተኪ አመራር ቋት ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡
5. በአመራር ቋት ውስጥ የገባ የተኪ አመራር ሊግ አባላት ቀጥሎ የሚኖረው አጠቃላይ እንቅስቃሴ በየደረጃው በሊጉ መዋቅር አማካኝነት ክትትል የሚደረግ ሆኖ በየ ሶስት ወሩ ተጠሪ ለሆነለት የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ሪፖርት መቅርብ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት- ከተኪ አመራር ቋት ስለመታገድ

1. ማንኛውም በተኪ አመራር ቋት የተያዘ አባል የአፈፃፀም ድክመት፤ የዲሲፕሊን ግድፈት፤ የብልሹ አሰራር እና የሰርጎ ገብነት ችግር ያለበት መሆኑ በግምገማ የተረጋገጠበት ከሆነ ከተኪ ቋት የሚታገድ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ አንድ አመራር በራሱ ፍቃድ ከአመራር ቋት ሊወጣ ይችላል።

## አንቀጽ አስራ ስምንት- ቅሬታ ስለማቅረብ እና የሚስተናገድ ሁኔታ

በየደረጃው በሚካሄደው የተኪ አመራር ቋት የማደራጀት ስራ ላይ ቅሬታ ያላቸው አባላት በብልጽግና ፓርቲ የአመራርና የአባላት የዲሲፕሊን መመሪያ የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታቸውን በማቅረብ መስተናገድ ይችላሉ።

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ- መመሪያውን ስለማሻሻል ወይም ስለመቀየር

ይህን መመሪያ በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሊያሻሽለው ወይም ሊቀይረው ይችላል።

**አንቀጽ ሃያ- መመሪያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከጸደቀበት ከ………….. ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

**ዐብይ አህመድ(ዶ/ር)**

**የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት**

**መያዚያ 2016 ኢ.አ**